**DISCIPLESHIP NETWORKING & ADVANCEMENT OF THE KINGDOM MINISTRIES**

DNA/DAN መጽሐፍ ቅዱሣዊ ደቀመዝሙርነትን፣ መንፈሣዊ ኅብረትንና በወንጌል ማዳረስ የክርስቶስን መንግሥት ማስፋትን ለማበረታታት በሕግ የተቋቋመ መንፈሣዊና ሰባዓዊ አገልግሎት ነው።

Website: http://www.DNAKingdomMinistries.org

(916)224-8939

hailetamirat@yahoo.com

አንደኛ ዓመት ቅጽ 1 June 2022

# ዜና DNA

DNA የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት በካሊፎርኒያ ሕግ ተመዝግቦ ሥራውን ከጀመረ ከስድስት ወራት ባይበልጥም፣ በነዚሁ ጥቂት ወራት የተሠራው ሥራ ሲታይ ግን በእርግጥም ራዕዩ ከእግዚአብሔር የመጣና ጌታ አምላክ ከፊቱ የወጣለት ለመሆኑ ጉልህ ምሥክር ነው።

ወደ ክንውን ዘገባዎቹ ከመግባቴ አስቀድሜ ስለ አገልግሎቱ አጀማርና ሥያሜ ጥቂት መግቢያ ልስጥ።

በ 2009 ዓመተ ምሕረት በአንድ ሁኔታ ምክንያት ከዚያ በፊት ጠይቄያቸው የማላውቃቸውን ጥያቄዎች እየጠየቅሁ የማሰላስልበት ጊዜ ነበረ። ዋናው ጥያቄ፡-

ክርስትናችን ምን ነካው? የሚል ነበር። በሁሉም አቅጣጫ ክርስትናችን ትምህርቱም የህይወት ልምምዱም (Practice) መዝመሙ ጎልቶ ታየኝ። ይህም በሁሉም የዓለም ክፍልና ማኅበረሰብ ነው። የአንዱ ማኅበረሰብ ከሌላው የሚለየው ቋንቋው ብቻ ሲሆን በይዘት ደረጃ ሁሉም ጋ ተመሣሣይና አንድ ነው። ፍጹም የተለየ ወንጌል እየተሰበከ ነው። የተለየ ትውልድም እየበቀለ ነው። የክርስትና ዕምነት መሠረት የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስ የሚተካ ሌላ መጽሐፍ ተጽፎ የተሠራጨ መሰለኝ። በምናቤ ያየሁት አዲሱ መጽሐፍም መጽሐፍ ቅዱሣችን "አይፈቀዱም" የሚላቸውን "ተፈቅዷል" የሚል፣ "አድርጉ" የሚለውን ደግሞ "አታድርጉ" ወይም "የማድረግ ግዴታ የለባችሁም" የሚል መጽሐፍ መሆን አለበት አልኩ። ይህንን መጽሐፍ በገበያ ላታገኙትና ምናባዊ ሊሆን ይችላል። ሥራውን ግን እየሠራ ነው።

በአጭሩ "ራስን መካድ፣ መስቀሉን መሸከምና ዕለት ዕለት ክርስቶስን መከተል" በሚል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተረጎመውና በአንድ ቃል ሲቀመጥ "ደቀመዝሙርነት" የተሠኘውን የሕይወት ልምምድ ሁሉም አውልቆ የጣለው መሰለኝ።

የዚህ ትምህርትና ልምምድ ከሕይወትም ከመድረክም በተግባራዊነቱ መጥፋቱ የክርስትናችን ማዝመም ዋና ምክንያት መሆኑ ገባኝ። የዕውነተኛ ደቀምዝሙርነት ተግባራዊ መገለጫዎችም፡-

1. የተለወጠ ሕይወት/በክርስቶስ ማንነትና ባሕሪይ የተቀረጸ ሕይወት
2. ጠንካራና ዕውነተኛ መንፈሣዊ ኅብረት/ፍቅር
3. ወንጌልን በመመስከር/በማዳረስ የክርስቶስን መንግሥት ማስፋት

   ይኼ በክርስቶስ ውስጥ የነበረና ወደ መጀመሪያው ምዕተ ዓመት አማኞች የተላለፈው የክርስቶስ ማንነት/ DNA/ ከቀጣዩ የክርስትና ትውልድ ቀስ በቀስ እየጠፋ መምጣቱና የአሁኑ ደግሞ ፈጽሞ የዕምነቱን ጀማሪ ክርስቶስንና የዕምነት አባቶቹን የማይመስል ለየት ያለ ትውልድ መሆኑ ቀድሞ ባልታየኝ ሁኔታ ግልጥ ብሎ ታየኝ።

   የአንድ ጸሐፊን አባባል ልዋስ፡-

   "የመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን አማኞች ማራኪ ሕወትና ወንጌልን የመስበክ ትጋት ሣያቋርጥ እስከ ዛሬ ቀጥሎ ቢሆን ኖሮ ዓለማችን ሃምሣ ጊዜ ያሕል ከዳር እስከ ዳር በወንጌል ትደረስ ነበር"

   ይኼ ሣይሆን በመቅረቱ ምክንያት የዓለማችን ¾ኛው ጥሬ/ድንግል መሬት ሆኖ ቀርቷል ወይም በሌሎች ዕምነቶች ቁጥጥር ሥር ይገኛል! መፈሣዊው DNA አልተላለፈማ!

**DNA** ሣይንሣዊ ቋንቋ እንደመሆኑ መጠን የመንፈሣዊ አገልግሎት መጠሪያ መሆኑ ግር ሊያሰኝ ይችላል፡፡ ለአገልግሎቱ ይህ ሥም የተሰጠበት ምክንያት ከትርጉሙ ጋር መንፈስ ቅዱስ ስላገጣጠመው ብቻ ነው፡፡

**DNA** በስነ-ሕይወት ሣይንስ፣ በማናቸውም ሕይወት ባላቸው ፍጥረታት ውስጥ የሚገኝና ማንነትን የሚለይ ንጥረ ነገር (Chemical) ሲሆን ይኼው ንጥረ ነገር የማንነት መለያ መረጃ (Genetic Information) ተሸክሞ ከወላጅ ወደ ልጅ ይተላለፋል፡፡ ይህንኑ ንድፈ-ሃሳብ (Theory) ወደ አገልግሎቱ ባሕሪይ ስናመጣው ደቀመዝሙርነት (Discipleship)፣ ሕብረት (Networking) ወንጌልን ማዳረስ (Advancement) በእግዚአብሔር (ሥላሴ) እና በአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን የነበረና ከትውልድ ወደ ትውልድ (Genetically) የሚተላለፍ ወይም ሊተላለፍ የሚገባው መንፈሣዊ ማንነት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በመሆኑም፣ ከየቃላቱ የመጀመሪያውን ፊደል ስንወስድ "DNA" የሚል ቃል/ሥም ይሰጠናል፡፡ " ሥምን መልዓክ ያወጣዋል" እንዲሉ የአገልግሎቱ ዋና ባሕሪይ እና ሥሙ ተገጣጥሞ ተገኘ፡፡

**DNA** የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት በካሊፎርኒያ ስቴት ሕጋዊ ፈቃድ ያገኘና በቤቴል ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን ባርኮት ለተቋቋመለት ዓላማ የተለየ መንፈሣዊና የማኅበረሰብ ልማት አገልግሎት ነው፡፡

**የDNA** ራዕይ፡- በክርስቶስ የሕይወትና የአገልግሎት ሞዴልነት የታነጹና በፍቅር ገመድ በአንድነት ተሣሥረው የወንጌሉን የምሥራች ላልሰሙ ለማሰማት የሚተጉ ደቀመዛሙርትን ያቀፉ ጠንካራ አብያተክርስቲያናት በዝተው ማየት ነው።

**የDNA** ተልዕኮ፡- ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መንፈሣዊና አካላዊ አንድነታቸውን እያጠነከሩ የዕሁድ መድረካቸውን ጨምሮ ጠቅላላው የእረኝነት እንክብካቤያቸው የአባላቶቻቸውን ሕይወት በደቀመዝሙርነት ባሕሪ በማነጽና መንፈሣዊ ትጥቅ አስታጥቀው ለወንጌል በማሠማራት ላይ እንዲያተኩሩ በትምህርትና በሥልጠና፣ እንዲሁም በምክርና በማቴሪያል ድጋፍ በማድረግ ታላቁን ተልዕኮ እንዲያሣኩ መርዳት ነው፡፡

**የDNA** ግብ፡- አዲስ ኪዳን በሚያስተምረን በነቢያትና በሐዋሪያት መሠረት ላይ በአንድነት የቆመች፣ የውስጥ ንጽሕናዋ መንፈስ ቅዱስን የሚማርክ፣ የውጭ ምሥክርነትዋ ደግሞ ዓለምን የሚማርክ፣ የነቢይነትና የክህነት ሚናዋን በተገቢው የምትጫወት፣ ተሰሚነትና አስሚነት ያላት የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ተገንብታና ለመነጠቅዋ ቀን ተዘጋጅታ ማየት ነው።

**DNA** የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት በ 2009 ዓመተ ምህረት ተጸንሶ በ 2019 የተወለደና በእግሩ ለመቆም እየታተረ ያለ መንፈሣዊና ልማታዊ ተቋም ሲሆን በቅርብና ሩቅ ትልሞቹ የሚከተሉት ተካተዋል፣

1. በአገልግሎቱ ጠያቂነትም ሆነ በአብያተክርስቲያናቱ ግብዣ በተከፈተው መድረክ ሁሉ የመጽሐፍ ቅዱሣዊ ደቀመዝሙርነትን ምንነት በትውልዱ ውስጥ በልዩ ልዩ መንገድ ማስረጽ ሲሆን ትኩረት የተደረገባቸው ትምህርቶችም፡-
    - የደቀመዝሙርነት ትምህርት
    - የአገልግሎት ትምህርት
    - የመዘምራንና የአምልኮ መሪዎች ሥልጠና
    - የጋብቻና ቤተሰብ ትምህርት
    - የመሪነት ትምህርት
    - የዓይነተኛ ቤተክርስቲያን ምንነት
    - የመንፈስ ኅብረት በአጥቢያ፣ በክልልና በአገር አቀፍ ደረጃ ለማጎልበት የሚረዳ ትምህርት
    - የጸሎት ትምህርት
    - የስልታዊ ወንጌል ሥርጭት ሥልጠና
    - ሌሎችም ለግል ህይወት ዕድገትና መንፈሣዊ መረዳትን ለማጎልበት የሚረዱ ትምህርቶች ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፡-
2. በየከተማውና በየአገሩ የኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን ቤተክርስቲያናት ኅብረት ባልመሠረቱበት እንዲመሠርቱ፣ ኅብረቶች ባሉበት ደግሞ እንዲጠናከሩ መርዳትና ማበረታታት፣
3. አብያተክርስቲያናትና የወንጌል አገልግሎት ተቋማት ወንጌልን ለማዳረስ በሚያደርጉ ጥረት ማገዝና ሚሲዮናዊ ተልዕኮ እንዲፋጠን ደጋፊ ኃይል መሆን እና፣
4. በገጠሮች አካባቢ የሚኖር ኅብረተሰባችን ንጹህ መጠጥ ውሀ እንዲያገኙ የተቻለውን ጥረት ከማድረግ ሌላ በጤናና በትምህርት መስክም ኅብረተሰቡን ለመርዳት የተቻለውን ለማድረግ ይጥራል።


የ DNA ራዕይ በልቤ የተጸነሰውና የተወለደውም በቤቴል ቤተክርስቲያን (ሣክራሜንቶ) እያለሁና እያገለገልኩ ሣለ በመሆኑ በራዕዩ ላይ ባርኮቷን እንድታሣርፍ December 14 እና 15 2019 በተደረገ ልዩ መርሀግብር ላይ የተገኙ አገልጋዮችና ምዕመናን በታላቅ ደስታ በእንባም ጭምር ነበር ሙሉ ድጋፋቸውን የገለጹት። ሁሉም እንደሚያስታውሰው ቀጣዩ ዓመት 2020 ዓለማችን አዲስ ዓይነት ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ የምታስተናግድበት ዓመት ሆነና የአገልግሎቱ ቀጣይ እርምጃ ለሁለት ሙሉ ዓመታት ተገታ!

እግዚአብሔር አምላክ በቸርነቱ ወረርሽኙን ባቀዘቀዘው ጊዜ እንደገና ከቆምንበት ለመነሣት በምናደርገው ዝግጅት የቤቴል ቤተክርስቲያን ምዕመናን የመጀመሪያውን የገንዘብ መዋጮ በማድረግ ዳግመኛ ጉዞ አስጀምረውናልና እግዚአብሔር አምላክ ይባርካቸው እላለሁ።

አገልግሎቱን ለአብያተክርስቲያናት ለማስተዋወቅና በሕግ ለማስመዝገብ ወደ ኢትዮጵያና ደቡብ አፍሪካ የተደረገ ጉዞ ታሪካዊ ነበር።

## ኢትዮጵያ





የአየር ጉዞ ወጪ ለመቀነስ ሲባል የተመረጠው የኳታር አየር መንገድ በመሆኑ ጉዞው ረጅምና አሰልቺ የነበረ ቢሆንም ከባለቤቴ ጽጌ ጋር ያደረግነው ጉዞ በመሆኑና ከሁሉም በላይ ጌታ አብሮን ስለነበርና ከፊታችን የሚጠብቀን የጌታ ሥራም ሠፊ እንደሆነ ስለምናምን በደስታ ነበር የተጓዝነው።

## አዲስ አበባ

በአብያተክርስቲያናት የነበረንን የአገልግሎት ጊዜ ሳንቆጥር የ DNAን አገልግሎት ለማስተዋወቅ የተደረገው መርሀግብር እጅግ ድንቅ ነበር።

አሥር ቤተዕምነቶችንና ሁለት ዋና ጽሕፈት ቤቶችን ለሚወክሉ ወደ መቶ የሚሆኑ መሪዎች በመሠረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ዋና ቢሮ የሕዝብ መሰብሰቢያ አዳራሽ ለሙሉ ቀን በተዘጋጀ ስብሰባ ላይ በመገኘት የግማሽ ቀን የአገልግሎት ሥልጠናና የግማሽ ቀን ደግሞ ራዕዩን የማስተዋወቅ መርሀ ግብር ተካሂዷል። ሥልጠናውም ሆነ ራዕይ የማጋራት መርሀ ግብሩ እጅግ እንዳስደሰታቸው የመርሀ ግብሩ ተሣታፊዎች በጥልቅ ስሜት

ሲገልጹ ስናይ ነገሩ ከጠበቅነው በላይ በመሆኑ እኛ ደግሞ ራዕይ የሠጠንንና በፊታችን ወጥቶ የመራንን አምላክ እጅግ አመስግነነዋል።





በአዲስ አበባ የተደረገውን የመሪዎች ሥልጠናና አገልግሎት የማስተዋወቅ መርሀ ግብር ተሣታፊዎች በከፊል

በመርሀ ግብሩ መጨረሻም፣ የ DNA አገልግሎት በኢትዮጵያ ሲመዘገብ የጠቅላላ ጉባኤ አባል ለመሆን ፈቃደኛ የሚሆኑ እስከ ሃያ ሰዎችን ስንጠይቅ ተሣታፊዎች ግር ብለው ወደ ፊት በመምጣት የአገልግሎቱ ደጋፊ ለመሆን ሲሸቀዳደሙ ስናይ ደስታችን ወደር አልነበረውም። የጠቅላላ ጉባኤ አባላትን በምንፈልገው ያህል ቁጥር ገድበን ከመዘገብን በኋላ የመጀመሪያ ዙር የ DNA ቦርድ አባላትን አስመርጠንና የቦርዱ ሥራ አስፈጻሚ አባላትም ተሰይመው ዕለቱ በታላቅ ስኬትና ደስታ ነበር የተጠናቀቀው። ከነዚሁ ተሣታፊዎች መካከልም የመጀመሪያ ዙር የ DNA/DAN አገልግሎት ቦርድ አባላት ተመርጠዋል



ኢትዮጵያ የ "DNA/DAN" ቦርድ አባላት የ DNA ን አገልግሎት ራዕይ፣ ተልዕኮና ግብ ምን እንደሆነ ለመግለጽና ስለመጽሐፍ ቅዱሣዊ ደቀመዝሙርነት ምንነት በተወሰነ ደረጃ ጥቆማ ለመስጠት የተጻፈና "ዲ ኤን ኤ -የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት" ባለ 230 ገጽ መጽሐፍም በዚሁ የመጀመሪያ ዙር አገልግሎቱን የማስተዋወቅ ወቅት ተመርቆ ለተሣታፊዎች ቀርቧል። የመጽሐፉ ሽያጭ የሚውለው ለአገልግሎቱ ድጋፍ ነው።

ነ




የመጽሐፉ ሽፋን

የኢትዮጵያው ቦርድ የአገልግሎቱን ሥያሜ በተመለከተ፣ በተለይ ከቅርብ ጊዜያት ወደዚህ "የመለኮት DNA ስላለብን እኛም አማልዕክት ነን" የሚል የተሣሣተ ትምህርት የሚያራምዱ አንዳንድ ክፍሎች በመኖራቸው በዚህ በኩል በመጋቢ ታምራት ኃይሌ DNA የተሰኘ አገልግሎት ተቋቋሟል የሚል ሲወጣ ለተሣሣተ ትምህርታቸው ተቀባይነት እንደ ግብዓት እንዳይጠቀሙበት ምን እናድርግ? በሚል በሠፊው ከተወያየን በኋላ ለጊዜው የDNAን ፊደሎች ቦታ ብቻ በመቀያየር የኢትዮጵያውን አገልግሎት DAN በሚል መቀጠል እንችላለን በሚል ስምምነት ላይ ተደረሰ።



የኢትዮጵያው አገልግሎታችን አስተባባሪ ው/ም ረታ ህብዶሎ ከባለቤቱና ልጆቹ ጋር

ቀጣዩ ጸሎትና ትኩረት አገልግሎቱን በኢትዮጵያ የሚያስተባብር ሰው መፈለግ ላይ ነበርና ከጥቂት ጊዜያት ጀምሮ በልባችን የነበረና በኅብረተሰብ ልማትና በመንፈሣዊ አገልግሎት ዙሪያ ሲሠራ የቆየ ወንድም ከነባለቤቱ ጠርተን ማነጋገር ነበረብን።በጣም አስገራሚው ነገር ታዲያ ይህም ወንድም በትክክል እግዚአብሔር ለዚህ ጥሪ ያዘጋጀው ሰው መሆኑን ካደረግነው ውይይትና አገልግሎቱን ለጊዜው በግማሽ ጊዜ ለማስተባበር ያደረግንለትን ጥሪ በፈቃደኛነትና በደስታ በመቀበሉ ጥሪው ከእግዚአብሔር መሆኑን ለማረጋገጥ ቻልን።

ቀጣዩ ተግባር ደግሞ ለአገልግሎቱ የሚሆን ቢሮ መፈለግ ነበር። ይህንኑ ጉዳይ ለመሐል አዲስ አበባ መሠረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን መሪዎች ስንገልጽላቸው ጥያቄውን በአፋጣኝና በደስታ ነበር የተቀበሉን። የመሐል አዲስ አበባ መሠረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ረዘም ላሉ ዓመታት አኔ በመጋቢነት፣ ባለቤቴም በዲቁናና በጸሎት ያገለገለችበት፣ ልጆቻችንም ተወልደው ድክ ድክ ያሉባት የአገልግሎት ቤታችን ስትሆን፣ የራሷ የሆነ የአምልኮ ቦታ እንዲኖራት አብረን ብዙ ደክመን ነበር። በአሁኑ ጊዜ ታዲያ ከአንድም ሁለት ቦታ ባለቤት ለመሆን እግዚአብሔር ያደላት ሲሆን በአንደኛው ቦታ ላይ ከገነባችው ባለ ዘጠኝ ፎቅ ሕንጻ ነው ለአገልግሎታችን የሚሆን ቢሮ ከፍት ያደረገችልን። ቦታውም በአዲስ አበባ ከተማ እጅግ ቁልፍና ምቹ በሚባል ከከፍተኛ ፍርድ ቤት ፊት ለፊት የሚገኝ በመሆኑ ለታዳጊው የ DNA አገልግሎት ምን ያህል ምቹና ደስታን የሚሰጥ መሆኑን ማንም ይረዳዋል።

የ DNA አገልግሎት ዋና ትኩረቱ የደቀመዝሙርነትን የባሕሪይና የአኗኗር መንፈሣዊ ግንባታ በቤተክርስቲያናት ውስጥ ማስረጽ ቢሆንም፣ በተወሰነ ደረጃ በሕብረተሰብ ልማት አስተዋጽዖ የሚያደርግ በመሆኑ ከመሐል አዲስ አበባ መሠረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ጋር በቅንጅት ለመሥራት ከታቀዱት አንዱ ከ HIV ጋር የሚኖሩ ቤተሰቦችን በኑሮ መደጎም በመሆኑ አሁን ለጊዜው ለአምሥት ቤተሰቦች በየወሩ የ $50 ዶላር ቀለብ ድጋፍ ተጀምሮላቸዋል



ከቤተክርስቲያኒቱ መሪዎች አንዱ ለተረጂዎች የተጀመረውን ድጎማ ጉዳይ ሲያስረዳ

ከአዲስ አበባ ክልል መሠረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ጽ/ቤት ኃላፊዎችም ጋር ተገናኝተን በቤተክርስቲያን ተከላ ጉዳይ ላይ ከተወያየን በኋላ አራት ያህል አገር በቀል ሚሲዮናውያንን ወንጌል ወዳልደረሰበት ዝግ ቦታ ለመላክ ተስማምተናል።



ከአዲስ አበባ ክልል መሠረተ ክርስቶስ ጽ/ቤት መሪዎች ጋር

ሌላው በ DNA ራዕይ ውስጥ የተካተተው ትልቅ ፕሮጀክት በሰሜን ኢትዮጵያ በዋግህምራ ዞን፣ በአበርገሌ ወረዳ በተለምዶ “የዛፍ ጥላ ትምህርት ቤቶች” የሚባል የትምህርት ሥርዓት(School system) ያለ ሲሆን እነዚህ “ትምህርት ቤቶች” ምንም ዓይነት ጣራና ግድግዳ ያለው ቤት በሌለበት ተማሪዎች በዛፍ ሥር ተቀምጠው የሚማሩበት ሥርዓት ነው። ይህንን ሁኔታ በአማራ ቴለቪዥን ካየሁበት ቀን አንስቶ ዕረፍት በማጣቴ ከፌዴራል ጀምሮ እስከ ወረዳው ትምህርት ቢሮ ኃላፊዎች ድረስ የመረጃውን ትክክለኛ ገጽታ ለማግኘት ጥረት አድርጌ በመጨረሻም ኃላፊዎቹን በባሕር ዳር ከተማ በአካል አግኝቼ ካነጋገርኩ በኋላ ይህንን አሣዛኝ ሁኔታ ለመለወጥ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የበኩላችንን አስተዋጽዖ ለማድረግ በቃል ደረጃ ተስማምተናል

በተገኘው መረጃ መሠረት አንዱን የ “ዛፍ ጥላ ትምህርት ቤት” ከአራት እስከ ስድስት ክፍል ኖሮት ወደ ዕውነተኛ ቤትነት ለመለወጥ የሚያስፈልገው የገንዘብ መጠን በብር እስከ 1,600,000.00 (USD $30,000) የሚያስፈልግ ሲሆን እኛም “የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል” (ነህ 2፡20) በሚለው ቃል ላይ በመመሥረት እነዚያ በዛፍ ጥላ ሥር ተኮልኩለው ያየናቸው ልጆች ጣራና ግድግዳ ውስጥ ተቀምጠው ሲማሩና የነገ ትውልድ ተረካቢ ሆነው ሲወጡ በዕምነት ዓይናችን እያየናቸው ነው። “ለእግዚአብሔር የሚሣነው ነገር የለምና” (ሉቃ 1፡37)



በአማራ ክልል የዋግህምራ ዞንና የአበርገሌ ወረዳ ትምህርት ቢሮ ኃላፊዎች

ከሰሜን ኢትዮጵያ ጉዞ መልስ ፊታችንን ያቀናነው ወደ ሆሣዕናና ብሎም ወደ ትውልድ ሥፍራዬ ኮዋዳ ነበር። የጥንቷ ኮዋዳ ከዋናዎቹ የኢትዮጵያ ኃይማኖቶች ውጭ ሥመ - ብዙ በሆኑ ባዕዳን አማልዕክት አምልኮ የተወረረች፣ ነዋሪዎቿም በድህነትና ኋላ ቀርነት ቀምበር ሥር የሚማቅቁና ጥቂት ጥሪት ቢኖራቸው እሷኑ ለዛር ለዉቃቢዎቹ ገብረው በረሃብ ይሰቃዩ የነበሩ ነበሩ።



የተወለድኩባት ቤትና ግቢ

በአውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር በ 1986 (በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1978) ዓመተ ምሕረት ከተወላጆቿ ከእኔ ቀጥሎ አራተኛ ታላቅ ወንድሜ የሆነው ኃይሉ ኃይሌ (አሁን መጋቢ) ከነቤተሰቡ ሁለተኛው የጌታ ምርኮኛ ሆኖና ራሱን ለወንጌል አገልግሎት ሰጥቶ ከወጣበት ጊዜ አንስቶ ነው የኮዋዳ ታሪክ የተቀየረው። ዛሬ በዚያ ጨለማ በነበረው ትውልድ መንደሬ ከ 36 ዓመታት በፊት የተተከለችው ቤተክርስቲያን የሰበሰበቻቸው ምዕመናን ብቻ ሳይሆኑ የወለደቻቸው ቅርንጫፍ (አጥቢያ) ቤተክርስቲያናትም ብዙ ናቸው ።

የመጀመሪያይቱ (እናት) አጥቢያም ትልቅ የማምለኪያ አዳራሽ የሠራች ቢሆንም በግንባታ ላይ በተሠራ ስህተት ምክንያት ግድግዳው ወደ ታች የመስመጥ አደጋ በማሣየቱ አፍርሣ

ለመሥራት በጠራችው ኮንፈረንስ ላይ ተገኝተን ለማገልገልና የአቅማችንን የገንዘብ አስተዋጽዖ ለማድረግ ነበር የሄድነውና በጊዜው የተቻለንን አድርገንና ለወደፊቱም የአቅማችንን ድጋፍ ለማድረግ ቃል ገብተን፣ በተጨማሪ በዚያ የሚገኘውን የቀለም ትምህርት ቤት ይዞታና የወደፊት አቅጣጫውንም በሚመለከት ምክክር አድርገን ተመልሰናል።



የኮዋዳ ቤተክርስቲያን ከውስጥ ሲታይ

ወደ አዲስ አበባ ከተመለስን በኋላ ቀጣዩ ሥራ ጋንዲ መታሰቢያ (የማዋለጃ) ሆስፒታልን መጎብኘት ነበረ። ጋንዲ ሆስፒታልን በተመለከተ በ DNA ራዕይ ውስጥ የተካተተ ጉዳይ አለ። በግምት ከሃያ ወይም ሃያ አምሥት ዓመታት በፊት በእረኝነት በማገለግልባት የመሐል አዲስ አበባ መሠረተክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባልና በዲቁና የሚያገለግል ወንድም ባለቤት ለወሊድ በገባችበት የማስተኛ አልጋ ስላልነበር በእስትሬቸር ላይ አስተኝተው ሲያንቀሳቅሷት ወድቃ ልጇን ከማጣቷም በላይ ወላዲቱም የተረፈችው በብዙ የሐኪሞች ጥረትና በእግዚአብሔር ቸርነት ነበር። ከዚህ ታሪክ ክስተት ጊዜ ጀምሮ የጋንዲ ሆስፒታል በልቤ እንደተረገዘ ይኖራል። እግዚአብሔር ጊዜው ደረሰና ዕድል ሰጥቶን ሆስፒታሉን ከመጎብኘታችንም በላይ የሆስፒታሉ ዳይሬክተር በጌታ ወንድማችን ሆኖ በመገኘቱ በልባችን ያረገዝነውን ታሪክ ለመጫወት ትልቅ ነጻነት አገኘን። ሆስፒታሉ በጠባብ በጀት የሚንቀሣቀስና የማዋለጃ አልጋዎች ከ 55 ዓመታት በላይ ያገለገሉ በመሆናቸው የረገቡና አንዳንዶቹም የተሰባበሩ ሆነው በማየታችን “ለካንስ ያየነውን ያሣየን ጌታ ነበር!” አልን።









ከላይ የምታዩት የሕመምተኛ መቆጣጠሪያም (Patient monitor) የተሰባበረና በፕላስተር የተያያዘ መሆኑን ልብ በሉ!

ለማንኛውም፣ አንድም ሆነ ሁለት፣ ሦሥትም ሆነ አራት የወላዶች አልጋ በዕርዳታ የምናገኝበትን መንገድ እንደምናፈላልግ ቃል በመግባት ለጊዜው ጉብኝታችን ፍሬያማ እንደነበር አምነን ወጣን።

DISCIPLESHIP
NETWORKING &
ADVANCEMENT
OF THE KINGDOM
MINISTRIES




የጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታል CEO ዶ/ር ታሪኩ ደሬሣ፣ እኔና ጽጌ

ወደ ካሊፎርኒያ (ሣክራሜንቶ) ከተመለስን በኋላ እነኚህን የማዋለጃ አልጋዎች በማፈላለግ ሂደት እንደተጠመድኩ በከተማችን በሚገኝ አንድ ሐኪም (ዶ/ር ኦላና አበራ የሚባል ) የቅርብ ወንድማችን አማካይነት ያገለገሉ የሕክምና መሣሪያዎችንና ቁሣቁሶችን ከሚለግስ ድርጅት ጋር የመገናኘት ዕድል አጋጠመኝ። ምንም ለጊዜው አልጋዎቹ በዕርዳታ ባይገኙም ሁለት አልጋዎችንና አምሥት የህመምተኛ መቆጣጠሪያዎች (Patient monitor) ከሌላ ቦታ በግዢ ተገኝቶ ተጨምሮበት አንድ ባለ 40 ጫማ (40 feet) ኮንቴይነር ሙሉ የሕክምና ቁሣቁሶችና መሣሪያዎች በመርከብ ተጭኖ ወደ ጇቡቲ ወደብ ተልኳል። ከለጋሽ ድርጅቶቹ ሌላ ወንድማችን ዶ/ር ኦላናን እንደዚሁም ከአንዴም ሦሥቴ ወደ ኦክላንድ ድረስ በመሔድ ቁሣቁሶቹን በማሸግና በኮንቴይነር በመጫን አድካሚውን ሥራ በደስታ የተወጡትን የሣክራሜንቶ ቤቴል ቤተክርስቲያን ወንድሞች ጌታ አምላክ ይባርካችሁ እላለሁ።

በዚህ ጭነት ከተካተቱት ውስጥ ጥቂቶችን መጥቀስ ቢያስፈልግ፡- ከማዋለጃ አልጋዎቹና የሕመምተኛ መቆጣጠሪያዎቹ (Patient monitors) በተጨማሪ እስትሬቸሮች፣ ዊልቼሮች፣ የሕጻናት አልጋዎች፣ የህመምተኛ የራስጌ ጠረጴዛዎች፣ ክራንቾች፣ ልዩ ልዩ መድኃኒቶችና መርፌዎች፣ ማስኮችና ጓንቶች፣ ሌሎች ብዛት ያላቸው ቋሚና አላቂ ቁሣቁሶች ይገኙበታል። ከነዚህ ቁሣቁሶች የተወሰኑቱ ለጋንዲ ሆስፒታል የታሰቡ ሲሆን አብዛኛዎቹ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ሰሜን ክልሎች በተደረገው ጦርነት ምክንያት ለወደሙ ሆስፒታሎች ማገገሚያ የሚውሉ ይሆናል



የሣክራሜንቶ ወንድሞችህ ዕቃዎቹን ሲያሰባስቡና ሲያሽጉ/በከፊል







ከላይ የሚታየው ለጉዞ የተዘጋጀው ኮንቴነር ነው።

በዚህ አጋጣሚ፣ ለኮንቴይነሩ መላኪያ ድጋፍ ለማሠባሰብ በተከፈተው “GoFundMe” አካውንት የገንዘብ ድጋፍ ላደረጉ ሁሉ በጌታ ሥም እና በነዚህ ቁሣቁሶች ተጠቃሚ በሆኑ ኢትዮጵያውያን ሥም እግዚአብሐር ይባርካቸው ለማለት እወዳለሁ።

**ደቡብ አፍሪካ**



ወደ ኢትዮጵያና ደቡብ አፍሪካ ጉዟችን ስንመለስ፣ የኢትዮጵያው ቆይታችን በመጠኑ ይህን ሲመስል ቀጣዩ ምዕራፍ በደቡብ አፍሪካ የተደረገ እንቅስቃሴ ነበረ። በደቡብ አፍሪካ የተወሰኑ ከተሞች ካደረግነው የአገልግሎት ጉዞዎች ሌላ ወንጌል አማኞች ቤተክርስቲያን በሚባለውና ወደ መቶ የሚጠጉ አጥቢያዎችን አቅፎ በቤተዕምነትነት በተደራጀው ቤተክርስቲያን ጆሃንስበርግ በሚገኘው ዋና ጽ/ቤቱ ከሁሉም አጥቢያዎቹ ለተውጣጡ መሪዎችና መጋቢዎች የሦሥት ቀናት የአገልግሎትና የመሪነት ሥልጠና ከሠጠን በኋላ በመጨረሻው ቀን የ DNA ን ራዕይና ተልዕኮ የማስተዋወቅ ጊዜ ነበረን። በዚህም ወቅት በኢትዮጵያ ያየነውን ዓይነት ልባዊና ደስታ የተመላበት አቀባበልና ድጋፍ አሣይተውናል።






በጆሀንስበርግ ወንጌል አማኞች ጽ/ቤት ሥልጠና ላይ የቆዩ መሪዎች በከፊል

ቀጥሎም ከዝቹ ከላይ ከጠቀስኳት የወንጌል አማኞች ቤተዕምነትና ከሌሎች ቤተዕመነቶች የተውጣጡ መጋቢዎችና ሌሎች መሪዎች በተገኙበት በፕሪቶሪያ ኬብሮን ቤተክርስቲያን አዳራሽ የተደረገው አገልግሎት የማስተዋወቅ መርሀግብር ልብ የሚነካ አቀባበል የታየበት ነበር። ሁሉም ተሣታፊዎች በሚባል ደረጃ በየተራ እየቆሙ ለራዕዩ ያላቸውን አድናቆትና በሁሉም ነገር ከራዕዩ ተልዕኮ ጋር ለመሰለፍ ያላቸውን ቁርጠኝነት ይገልጹ ነበር። በመጨረሻም በደቡብ አፍሪካ አገልግሎቱን የሚመራ 12 አባላት ያሉት ጠንካራ ቦርድ ተቋቁሞና አገልግሎቱን በግማሽ ግዜ የሚያስተባብር አገልጋይ ሹመት ተካሂዶ መርሀ ግብሩ በድል ተጥናቋል።

በጆሃንስበርግ የሚገኘው የወንጌል አማኞች ቤተዕምነትም በዋና ጽ/ቤቱ ሕንጻ አንድ ቢሮ በነጻ ማበርከቱ ሌላው ታላቅ በረከት ሲሆን፣ የደቡብ አፍሪካው ቦርድ ለየት ያለ እርምጃ ደግሞ የቦርድ አባላቱ ለአገልግሎቱ ማስጀመሪያ ዘር ይሁን በሚል ገንዘብ አዋጥተው በኢትዮጵያ አንድ የወንጌል መልዕክተኛ በ DNA አገልግሎት ሥም ለመላክ መወሰናቸው ነበር።



የደቡብ አፍሪካው ቦርድ አባላት

የደቡብ አፍሪካው የ DNA ጅምር አገልግሎትም በኢትዮጵያው ቦርድ የተሰጠውን አስተያየት በመንተራስ የአገልግሎቱ ሥም "DAN" ተብሎ እንዲመዘገብ ወስኖ እንቅስቃሴውን በሚያስገርም ሁኔታ የጀመረ ሲሆን በጆሃንበርግ አካባቢ ለረጅም ጊዜ በመጋቢነት ያገለገለው ፓስተር ሙሉቀን አያልነህ የአገልግሎቱ የከፊል ጊዜ አስተባባሪ ሆኖ ተሠማርቷል።



ፓስተር ሙሉቀን አያልነህ ከባለቤቱና ልጆቹ ጋር

የደቡብ አፍሪካው ቲም በሰብሣቢው ቢሾፕ አዳነ አሻሞና በምክትል ሰብሣቢው ቢሾፕ ተገኝ አቡቴ አንቀሣቃሽነት ከአስተባባሪው መጋቢ ሙሉቀን አያልነህ ጋር እጅግ በሚያስገርም ሁኔታ ወደ ፊት እየሮጡ ነውና ለደስታዬና ለምሥጋብናዬ ወደር እንዳይኖረው አድርገዋልና የሥራው ባለቤትና የእረኞች ዓለቃ የሆነው ጌታ ይባርካቸው ለማለት እወዳለሁ።

"ከድሮ ዘመን የፈረሱት ሥፍራዎች ይሠራሉ፣ የብዙ ትውልድም መሠረት ይታነጻል" (ኢሣ 58፡12)

ማራናታ!

የደቡብ አፍሪካዋ ራስተንበርግ ከተማ




በደቡብ አፍሪካ ራስተንበርግ የወንጌል አማኞች አጥቢያ መዘምራን ከሥልጠና በኋላ



ጽጌም እህቶችን በማማከርና በጸሎት በመርዳት ተልዕኮውን ተካፍላለች

በዚህች በራስተንበርግ ከተማ ጌታ ከሠራው ድንቅ ሥራ የመጀመሪያ የሚሆነው በከተማይቱ አማኞች መካከል በሰው ሕይወት መጥፋት ዙሪያ በወገኖች መካከል ለዓመታት ነግሦ የቆየ ጠላትነትና በክፉ መፈላለግ በዕርቅ ተወግዶ ተፈላላጊዎቹ በሕዝብ ፊት ተናዘውና ይቅርታ ተጠያይቀው ሲተቃቀፉ የተገለጠውን የእግዚአብሔር መንፈስና ክብር በቃላት መግለጥ ያዳግታልና ለጌታ ብቻ ክብር ይሁንለት!!!

እንግዲህ፣ በኢትዮጵያም ሆነ በደቡብ አፍሪካ ልዩ ልዩ አብያተክርስቲያናት ለኮንፈረንሶችና መሰል ስብሰባዎች ያደረግናቸው የአገልግሎት ጉዞዎች ሳይቆጠሩ ከ DNA የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት ጋር በተያያዘ ብቻ የተደረጉ እንቅስቃሴዎችን ከምላ ጎደል ለመዘርዘር ሞክሬአለሁ።

በጥቅሉ፣ ያለፉት ሥድስት ወራት ከ DNA የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት አኳያ ታላላቅ የመሠረት ሥራዎች የተሠሩባቸው ወራት ሲሆኑ ከ April 22-24 በ አትላንታ ግሎባል ቤተክርስቲያን በተደረገ ኮንፈረንስ ላይ ከተደረገልኝ የአገልግሎት ግብዣ በተጨማሪ ስለ አገልግሎቱ ገለጻ ማድረግ ትችላለህ በመባሌ በኮንፈረንሱ ማጠቃለያ ዕሁድ ላይ በጽሁፍ የተደገፈ ገለጻ አድርጌ የነበረ ሲሆን የመሪዎቹም ሆነ የምዕመናኑ አቀባበል እጅግ የሚባርክ ነበረ። በዚህ አጋጣሚ የቤተክርስቲያኒቱን መጋቢዎችና ሽማግሌዎች እግዚአብሔር ይባርኳችሁ ለማለት እወዳለሁ።

ኮንፈረንሱ ካለቀ በኋላ ባለው ሰኞ ደግሞ በአትላንታ ከተማ የሚገኙና ወደ 11 የሚሆኑ ቤተክርስቲያናት መጋቢዎች በተሰበሰቡበት ተመሣሣይ ገለጻ የተደረገ ሲሆን መጋቢዎቹ በግላቸውም ሆነ በቤተክርስቲያናቸው ደረጃ ከአገልግሎቱ ጎን እንዲቆሙ ጥሪ ቀርቦላቸው በመልካም መንፈስ ተቀብለውታል። በተጨማሪም ምቹ በሆነ ጊዜ በከተማይቱ አገልግሎቱ የሚተዋወቅበትን መድረክ በኅብረት እንደሚያመቻቹም ቃል ገብተዋል። መጋቢዎቹን በሙሉ በአገልግሎቱና በራሴ ሥም እግዚአብሔር አምላክ ይባርካቸው ለማለት እወዳለሁ።

እግዚአብሔር ለእስራኤል ቤት ከተናገረው መልካም ነገር ሁሉ ተፈጸመ እንጂ ምንም አልቀረም።
**መጽሐፈ ኢያሱ 21:45**
There failed not ought of any good thing which the LORD had spoken unto the house of Israel; all came to pass.
**Joshua 21:45**

**ቀጣይ የቅርብ ጊዜ ዕቅድ**

በኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ቦታዎች ለመሪዎችና በልዩ ልዩ አገልግሎት ዘርፍ ለተሠማሩ ሥልጠና ለመስጠትና አገልግሎቱን በተግባር ለመጀመር፣ እንደዚሁ የጸጥታ ሁኔታ ከፈቀደም በአማራ ክልል ሰሜን ወሎ ዋግህምራ ዞን የዛፍ ጥላ ትምህርት ቤቶችን ወደ መደበኛ ቤትነት ለመለወጥ የሚያስችል ሥራ ለመጀመር በመጪው ሐምሌ ወር ሁለተኛ ዙር ጉዞ አደርጋለሁ።

በደቡብ አፍሪካም ወደ 6 ቦታዎች ላይ ሠፋፊ የመሪዎች ሥልጠናና የወንጌል ስብከት ኮንፈረንሶች በተለያዩ ዞኖች መዘጋጀታቸውን በዚያ ያለው የአገልግሎቱ ቦርድ አስታውቀውኛል። በተለይ በደቡብ አፍሪካ ያለን ተልዕኮ ሥራና የተሻለ ኑሮ ፍለጋ በአየር፣ በየብስና በባሕር ላይ ጉዞ እንደ ጎርፍ የሚጎርፈውን ስደተኛ ሕይወት በወንጌል ለመታደግ የተከፈተ በር በመሆኑ እንደቀላል አናየውም።

**እንግዲህ፣ ከላይ የተዘረዘሩ ጅምሮችን ወደፊት ለማስኬድ፣ ለአስተባባሪዎች መንቀሣቀሻ ክፍያ፣ ለቢሮ ኪራይ (በኢትዮጵያ)፣ ለ HIV ህሙማን ተረጂዎች ክፍያ፣ ከሥልጠናዎች ጋር በተያያዘ ለአዳራሽ ኪራይ፣ ለመስተንግዶ፣ ለማቴሪያሎች ማባዣ፣ ለድጋፍ ሰጪ አገልጋዮች፣ ለትራንስፖርትና የሆቴል ወጪዎች የሚሆን ድጋፋችሁን ከታች በተዘረዘሩት የመስጫ ዘዴዎች በመጠቀም በመለገስ የተለመደ ትብብራችሁን እንድታሣዩንና ይህንን ሠፊ ሥራ አብረን እንድንሠራ ግብዣችንን በአክብሮት እናቀርባለን**

**በቼክ ከሆነ በ 8108 Montevina drive Sacramento, CA 95828 አድራሻ ይላኩ**

**(ቼክ ሲጽፉ "DNA Kingdom Ministries" ማለቶን አይርሱ)**

**PayPal ከሆነ፣ DNAKingdomMinistries@gmail.com**

**CASH APP ከሆነ፣ DNAKingdomMinistries@gmail.com**

**Zelle ከሆነ፣ DNAKingdomMinistries@gmail.com**

**ልዩ አስተያየት ወይም ጥያቄ ካለዎት በ (916) 224-8939 ይደውሉልን**

***"ከድሮ ዘመን የፈረሱት ሥፍራዎች ይሠራሉ፣ የብዙ ትውልድም መሠረት ይታነጻል" (ኢሣ 58፡12) ማራናታ!!!***

ዜና DNA/DAN አገልግሎት ቅጽ 1